**Ethiopian Journal of Business and Social Science**

**DOI:** https://doi.org/10.59122/154F53lu

**Volume: 6 Number: 2 , 2023 , Pages: 82~107**

**ISSN:2707-2770**

# በትምህርታዊ ጨዋታዎች የማንበብን ክሂል ማስተማር የተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነት የማሳደግ ሚና ፍተሻ፤ አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ በሚማሩ የ5ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት

**በወንድማገኝ አደም**

Email: mukeremwonde@gmail.com

**አማካሪዎች፡- ዶ/ር ጌታቸው እንዳላማው፡** Email: get_end_asf@yahoo.com እና

**ዶ/ር ግርማ ገብሬ፡** Email: girma62@yahoo.com

***Article Info***

*Accepted on September, 2023*

*Published on: December, 2023*

***©Arba Minch University, all rights reserved***

***አጠቃሎ***

*የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ትምህርታዊ ጨዋታዎችን ተጠቅሞ የማንበብ ክሂልን ማስተማር በተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት ላይ ያለውን ሚና መመርመር ነው። ጥናቱ ፍትነት መሰል የምርምር ንድፍንየተጠቀመ ሲሆን አንድ የቁጥጥር ቡድን እና አንድ የሙከራ ቡድን የያዘ ነው። በእየቡድኑ 35 ተማሪዎች በጠቅላላ 70 ተማሪዎች ተሳትፈዋል። አጥኚው የጥናቱን በታና ምድቦችን በአመቺ ንሞና ስልት፤ የክፍል ደረጃን(5ኛ ክፍልን)እና መምህርመረጣን በዓላማ ተኮር ንሞና፤ የጥናቱ ተሳታፊዎችን ደግሞ በጠቅላይ የንሞና ስልት መርጧል። በመረጃ መሰብሰቢያነትም የቅድመ ትምህርትና የድህረ ትምህርት የማንበብ ተነሳሽነት ደረጃ መለኪያ የጽሁፍ መጠይቆችን ተጠቅሟል። ትምህርቱ ለ16 ሳምንታት የተሰጠ ሲሆንአጥኚው የሁለቱ ቡድን የማንበብ ተነሳሽነት ውጤቶችንተዛምዶ ለመለየት የፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ቀመርን ተጠቅሟል። በተጨማሪም የነፃ ናሞና ቲ-ቴስት ስታትስቲካዊ መተንተኛ ስልትን በመጠቀም በእየቡድኖቹ የተገኘው የቅድመና ድህረ ትምህርት አማካይ፣ መደበኛ ልይይትና የጉልህነት መጠናቸው ተሰልተው ተተንትነዋል።ውጤቱም የቅድመትምህርቱ የተዛምዶ መጠን (r= .067)እና የቁጥጥር ቡድኑ አማካይውጤት(M=51.29)፣ የሙከራው(M= 50.54)ሲሆን፤የጉልህነት ደረጃውም(P= .581) በመሆኑ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን አሳይቷል። በአንፃሩ በድህረትምህርቱ የታየው የተዛምዶ መጠን(r= - .306) የድህረትምህርቱ አማካይ ውጤት የቁጥጥር ቡድኑ(M=51.77)፣ የሙከራው(M= 55.06) ሆኖ ተገኝቷል። የጉልህነት መጠኑም (P= .010) በመሆኑ በሁለቱ ቡድኖች የማንበብ ተነሳሽነት ደረጃ መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን አመላክቷል።*

**ቁልፍ ቃላትና ሀረጋት :** ትምህርታዊ ጨዋታ፣ የተለመደ የማስተማር ስልትና የማንበብ ተነሳሽነት

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ሁለተኛ ቋንቋን በማስተማር ሂደት አንዱና ዋነኛው ተግዳሮት ተማሪዎችን በመማሩ ሂደት ውስጥ ተሳትፏቸውንና የመማር ፍላጎታቸውን ማስጠበቅ መቻል ነው(Gardner, & Lambert: 1972)፡፡ ከተማሪዎቹ ውጤታማና መልካም ምላሽ ለማግኘት መምህራን የተማሪዎቻቸውን ስነልቦናዊ ባህሪና ተጽእኖ አድራሽ ነገሮችን (ለምሳሌ ተነሳሽነታቸውን፣ ጭንቀታቸውንናበራስየመተማመን ሁኔታቸውንበመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ መረዳት አለባቸው(Krashen: 1982)፡፡ የሁለተኛም ሆነ የውጭ ቋንቋን እውቀትና ክሂልን ለማዳበር ከተፈለገ በማንበብ ክሂል የተሻሉ ሆኖ መገኘት ያስፈልጋል (Demirel, 2003)፡፡ ምሁሩ አያይዘውም ማንበብ በዓለም ላይ ስለሚከናወኑ ሁነቶች ያለንን ግለሰባዊ እውቀትም ሆነ ማንነታችንን ለሌሎቹ ለማሳወቅና የሌሎችንም ማንነት ለመረዳት ማስተሳሰሪያ ገመድ በመሆን ሰፊ አገልግሎትን እያበረከተ ያለ የክሂል ዘርፍ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

(Guines, 1997) ማንበብ ከሌሎች ክሂሎች በተለየ ሁኔታ ውስብስብ ክንዋኔዎች ተቀናጅተው ወጥ ተግባርን የሚፈጽሙበት ሂደት መሆኑን በመጠቆም የማንበብን ክሂል ውስብስብ ከሚያሰኙት ጉዳዮች ውስጥም ሰው ንባብን በሚያነብበት ወቅት በርካታ አእምሯዊ ሂደቶች ተቀናጅተው ይሳተፋሉ፡፡ ለምሳሌ ሽምደዳ ወይም ማስታወስ፣ ትኩረት፣ አድምጦ መገንዘብ እና ከፍተኛ የሆነ የቋንቋ አጠቃቀም ችሎታ የሚሉት በማንበብ ወቅት በጋራ ከሚከሰቱት ክንውኖች ውስጥ ተጠቃሽ ናቸው በማለት ገልጸዋል፡፡ Akyol (2011) እና Baker & Wigfield (1999) በበኩላቸው በማንበብ ተግባር ከሚያገለግሉ አእምሯዊ ሂደቶች ውስጥ የስሜታዊ አሠራር ስልቶች /emotional mechanisms/ በአይቀሬነት የሚከሰቱ ሁነቶች ሲሆኑ ከእነዚህም አንዱ ተነሳሽነት መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ እንደምሁሮቹ ገለፃ ማንበብ ተነሳሽነትን የሚፈልግ የሆነ ሰዎች አንድን ድርጊት ለመፈፀምም ሆነ ላለመፈፀም የሚያግዝ ገፋፊ ኃይል ነው፡፡ ይህም ማለት ተማሪው ጠንካራ አእምሯዊ ብቃት ቢኖረውምእንኳ ለማንበብ በቂ የሆነ ተነሳሽነት ከሌለው የማንበቡ ተግባር ውጤታማ ሊሆን አይችልም፡፡ በመሆኑም ተነሳሽነት ለሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ ክሂል መዳበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው (Grabe, 2009; Grabe & Stoller, 2011)፡፡ ቀጥተኛ የሆነ ፍላጎት የሌለበት መማር ተማሪውን ወደ መደናገር እና አላስፈላጊ ጫና ውስጥ እንደሚያስገባውና በአንፃሩ አንድን ነገር ለመማር ፍላጎት ያለውተማሪስለሚማረው ነገር እውቀትም እምነትም እንደሚኖረው Wang (2018) ያስረዳሉ፡፡ በተመሳሳይ Yu, et al. (2021) እንደገለጹት ትምህርታዊ ጨዋታዎች ከፍተኛ ጥራት ያለው ትምህርትን ለማስተማር የሚያስችል ኃይል ያላቸው፣ በንጽጽር ሲታይ ቀላል ወጪን የሚጠይቁ፣

ከሁኔታዎች ጋር ተለዋዋጭ (flexible) የሆነ አውድን ለመፍጠር የሚያስችሉ፣ አመቺ የትምህርት አገልግሎትን ለመስጠት የሚያስችሉ፣ ከማስተማሪያ መሳሪያዎችም ሆነ ከተማሪዎች እንዲሁም መምህራን ጋር በቀላሉና በፍጥነት ለመግባባት እድልን የሚፈጥሩ የማስተማሪያ ስልት መሆናቸውን አብራርተዋል፡፡በተጨማሪም ትምህርታዊ ጨዋታዎች የተማሪዎችን አካላዊም ሆነ ስሜታዊ መጨናነቆችን የሚያረግቡና በአንፃሩ ነጻነት እንዲሰማቸው የሚያደርጉ የሁለተኛም ሆነ የውጭ ቋንቋዎች ማስተማሪያ ስልት ናቸው (Hariri, 2014)፡፡ ለአብነትም የሁለተኛ ቋንቋን በትምህርታዊ ጨዋታ ማስተማር በተለመደው ስልት ከማስተማር የተሻለ ውጤታማ እንደሚያደርግ በጥናት ያመላከቱት Aldabus (2008) ናቸው፡፡ አልዳቡስ በሊቢያ ዋና ከተማ ትሪፖሊ እንግሊዝኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎችን በሁለት ቡድን ከፍለው እንዲማሩ አድርገዋል፡፡ በጥናታቸው ውጤትም በትምህርታዊ ጨዋታ ስልት የተማሩ ተማሪዎች የተሻለ ውጤት ያሳዩ ከመሆኑም በተጨማሪ መምህራን ባስተዋሉት አዲስና ውጤታማ የማስተማሪያ ስልት የተማሪዎችን የተሳትፎ ተነሳሽነት ከበፊቱ በተለየ ሁኔታ ጨምሮ ማየታቸውን አረጋግጠዋል፡፡

Boctor (2013) በተመሳሳይ፣ በሁለተኛም ሆነ በውጭ ቋንቋዎች ማስተማር ወቅት ትምህርታዊ ጨዋታዎችን ተጠቅሞ ማስተማር በቀዳሚነት የተማሪዎችን የመማር ተነሳሽነት እንዲጨምር ያግዛል፡፡ በተጨማሪም ይህንን ተነሳሽነት ተጠቅመው በመማር ማስተማሩ ላይ ያላቸውን ተሳትፎ የማስተባበር አቅማቸውን እንዲሁም የፈጠራ ችሎታቸውን እንደሚያሳድግ ገልጸዋል፡፡ በተመሳሳይ Taghizadeh, et, al. (2017) ትምህርታዊ ጨዋታዎችን ተጠቅሞ ቋንቋን ማስተማር በተለመደው ስልት ከማስተማር በተሻለ ሁኔታ የቃላት ፍችን በቀላሉ እንዲያውቁ እንደሚረዳ ጠቅሰዋል፡፡ በአንፃሩ እንደ Guthrie et al. (2006) Guthrie & Wigfield (2000) Wang and Guthrie, 2004) ያሉ ምሁራን የማስተማሪያ ስልቶችን በመቀያየር የተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነት ማዳበር እንደማይቻልና ይልቁንም በራሳቸው በተማሪዎች ታላሚውን ቋንቋ ለመማርና ለማንበብ ባላቸው ውስስጣዊ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናት አዘጋጅ ከኢትዮጵያ አውድ አንፃር አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ የ5ኛ ክፍል ተማሪዎችን ትምህርታዊ ጨዋታዎችን ተጠቅሞ የማንበብ ክሂልን ማስተማር በተለመደው ስልት ከማስተማር የተለየ በተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት መዳበር ላይ ያለውን ጉልህ ሚና ለመለየት ፍትነት መሰል ጥናት አካሂዷል፡፡

### 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ችግር

በውጭው ዓለምም ሆነ በኢትዮጵያ የተማሪዎች የማንበብ ባህል በጣም ዝቅተኛ መሆኑን በዘርፉ ጥናት ያደረጉ አካላት በተለያዩ ጊዜያት በተደረጉ ጥናቶቻቸው አስገንዝበዋል፡፡ ለአብነትም በውጭው ዓለም Namanziandost et al. (2022) የማንበብ ክሂል መዳበር ማንኛውንም ቋንቋ ለመማር ወሳኝ መሆኑን በማስታወስ (Dar et al., 2019; Endris, 2018; Rafiq et al., 2019) እንዲሁም Sajid et al., 2019)ን ዋቢ አድርገው እንደገለጹት የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎችን አስመልክቶ በተደረጉ ጥናቶች የሁለተኛ ቋንቋን የማንበብ ባህላቸው በጣም ደካማ መሆኑን አመላክተዋል፡፡ ለዚህም እንደምክንያት የጠቀሱት ተማሪዎች የሚያነቡት ለፈተና ውጤት ሲሉ ብቻ በመሆኑ ከፈተና በፊትም ሆነ ከፈተና በኋላ ግን የማንበብ ፍላጎት የሌላቸው መሆኑን በጥናት ማረጋገጣቸውን ጨምረው ጠቅሰዋል፡፡

የማንበብ ተነሳሽነት ግለሰባዊ የሆነ ዓላማ ያለው ተማሪዎች የሚነበበውን ርእስ መሠረት አድርገው ስለማንበብ ያላቸው አዎንታዊ ወይም አሉታዊ የሆነ ሃሳብ እና ስሜት ማለት ነው (Guthrie & Wigfield, 1997, 2000)፡፡ አያይዘውም ምሁራኑ ይህ ግለሰባዊ ልዩነትም የሚመጣው በአውዶች መለያየት (በመኖሪያ ቤት ሲሆኑ፣ ትምህርት ቤት ሲሆኑ፣ በጽሁፉ ዓይነት ይህም ሲባል መረጃ ወይስ ታሪክን ይዟል?) በሚለው ምክንያት እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ Deci et al. (2001) ሲገልጹ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማሳደግ የማንበብ ተነሳሽነት ወሳኝ ሚና ያለው መሆኑ ቢታመንበትም ተነሳሽነት በራሱ የተማሪዎችን ስነልቦናዊ እና አእምሯዊ ዝግጁነት ለማንበብካላቸው መልካም ፈቃደኝነት ጋር ማስማማትን ይጠይቃል፡፡ ይህ የተማሪዎች የማንበብ ፈቃደኝነትም በራሱ ከተማሪዎቹ አቅም በላይ በሆኑ የተለያዩ ውጫዊ ተጽእኖዎች እንደሚወሰን ያስረዳሉ: ይህምበመሆኑ የተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነት የሚያደናቅፉ ችግሮችን አስመልክቶ ምሁራን በእየራሳቸው ጎራ ተከፋፍለው አከራካሪ ሃሳባቸውን ሰንዝረዋል፡፡

ለአብነትም የውጭም ሆነ የሁለተኛ ቋንቋን የማንበብ ክሂል ትምህርት በተለመደው ስልት ከማስተማር ይልቅ በትምህርታዊ ጨዋታ ስልት ማስተማር የተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነት ያዳብራል የሚል ሃሳብከሚያራምዱት ውስጥ Guthrie et al. (2007) አንዱ ናቸው፡፡ Maduk et al (2017) በበኩላቸው ትምህርታዊ ጨዋታ በትምህርት ወቅት እንደጣልቃገብና አዘናጊ ጉዳይ ሳይሆን መታየት ያለበት የተማሪዎችን ተነሳሽነት ከመጨመር አኳያ የላቀ ጠቀሜታ እንዳለው በመገንዘብ በንቃት ወደቀረበላቸው የትምህርት ይዘት የሚያስገባ ስልት መሆኑን መረዳት እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል፡፡

በተቃራኒው Shanahan (2019) (Brofi, 2010 and Jakuz, 2001)ን ዋቢ አድርገው እንደገለጹት እንዲሁም Guthrie et al. (2006), Guthrie & Wigfield (2000), Wang and Guthrie: 2004) ያሉ በዘርፉ ጥናት ያካሄዱ ምሁራን ደግሞ የተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት የሚወሰነው ከማስተማሪያ ስልቱ መቀያየር ይልቅ ራሳቸው ተማሪዎቹ ለሚያነቡት ጽሁፍ በሚሰጡት የጊዜ፣ የትኩረት፣ የመስዕዋትነት፣ በአጠቃላይም በእነሱ ፍላጎትና አመለካከት ተጽእኖ ሥር መሆኑን የሚያስረዳ ሃሳብን ያራምዳሉ። ምሁራኑ ለዚህ ተቃውሟቸው እንደማስረጃ የሚያቀርቡት ሃሳብ ተማሪዎች የሁለተኛም ሆነ የውጭ ቋንቋን በሚማሩበት ጊዜ ራሳቸው ታላሚውን ቋንቋ በሙሉ ፍላጎትና አትኩሮት ለማንበብና ለመማር እስካልተነሳሱና ጥረት እስካላደረጉ ድረስ በሌላ ውጫዊ ማነቃቂያ ተጽእኖ ሊወዱትና በተነሳሽነት ሊያነቡት፣ ሊማሩት ብሎም ውጤታማ ሊሆኑ አይችሉም የሚል ነው። በአጠቃላይ ከላይ በቀረበው ጽሁፍ በአሁኑ ወቅት በውጭው ዓለም የተማሪዎች የማንበብ ፍላጎትም ሆነ ችሎታ ዝቅተኛ መሆኑና እንደመፍትሄም በተወሰኑ የውጭ ተመራማሪዎች (ለምሳሌ ከለይ በጥናቱ ዳራ በAldabus, 2008; Boctor, 2013; Taghizadeh et al., 2017) ትምህርታዊ ጨዋታዎች የማንበብ ተነሳሽነትን ለማዳበር ከተለመደው የማስተማሪያ ስልት የተሻሉ መሆናቸው ተገልጿል። በአንፃሩ የማንበብ ተነሳሽነትን ለማሳደግ ትምህርታዊ ጨዋታዎችን ጨምሮ ሌሎች የማስተማሪያ ስልቶችን መቀያየር መፍትሄ እንደማይሆን የሚከራከሩ አካላት በመኖራቸው ምክንያት አወዛጋቢ ሃሳቦች መኖራቸውንም አጥኚው በጥናቱ አነሳሽ ችግር ሥር ከተጠቀሱ ሃሳቦችተገንዝቧል፤ ባደረገው ክለሳ ድርሳናትም በአገራችን በትምህርታዊ ጨዋታ ማስተማርን በተመለከተ የተደረጉ ጥናቶች አላጋጠመውም። በመሆኑም እነዚህን ችግሮች ግምት ውስጥ በማስገባት አጥኚው ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር በ2015ዓ.ም አማርኛ ቋንቋን እንደሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ የወሽቅን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትቤት የ5ኛ ክፍል ተማሪዎችን የማንበብ ክሂል ትምህርት በትምህርታዊ ጨዋታ ስልት ማስተማር በተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት ላይ በተለመደው የማስተማሪያ ስልት ከማስተማር የተለየ ጉልህ ሚና መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ ፍትነት መሰል ጥናት አካሂዷል። ጥናቱም የሚከተሉትን መሠረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክሯል።

አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎችን የማንበብ ክሂል ትምህርት

1. በትምህርታዊ ጨዋታ ስልት ማስተማር ከተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት ጋር ከተለመደው ስልት የተለየ ግንኙነት አለውን?
2. በትምህርታዊ ጨዋታ ስልት ማስተማር በተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት ደረጃ ላይ በተለመደው ስልት ከማስተማር የተለየ ጉልህ ልዩነት አለውን?

### 1.3 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ የ5ኛ ክፍል ተማሪዎችን የማንበብ ክሂል ትምህርት በትምህርታዊ ጨዋታ ስልት ማስተማር በተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት ላይ ያለውን ጉልህ ሚና መመርመር ነው።

### 1.4 የጥናቱ መላምቶች

ይህ ጥናት ከዚህ በታች የተጠቀሱትን አልቦ መላምቶች በመፈተሽ የተማሪዎችን የማንበብ ክሂል ለማዳበር የትምህርታዊ ጨዋታ ስልት ከተለመደው የማስተማር ስልት በተለየ ጉልህ ሚና ያለው መሆን አለመሆኑን መርምሯል።

አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎችን የማንበብ ክሂል ትምህርት

1. በትምህርታዊ ጨዋታ ስልት ማስተማር ከተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነትጋር ከተለመደው ስልት የተለየ ግንኙነት የለውም።
2. በትምህርታዊ ጨዋታ ስልት ማስተማር በተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት ደረጃ ላይ በተለመደው ስልት ከማስተማር የተለየ ጉልህ ልዩነት የለውም።

### 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት መካሄዱ በተለይም ለሁለተኛ ቋንቋ መምህራን የማንበብን ክሂል ትምህርት ለተማሪዎች ሳቢና አዝናኝ እንዲሁም አሳታፊ በሆነ ትምህርታዊ ጨዋታ ስልት ማስተማር በተለመደው ስልት ከማስተማር በተሻለ የማንበብ ተነሳሽነታቸውን እንደሚያዳብርላቸው ግንዛቤን ይሰጣል ተብሎ ይታሰባል። እንዲሁም በትምህርታዊ ጨዋታዎች ማስተማር በተለመደው ስልት ከማስተማር በተሻለ የተማሪዎችን እኩል ተሳታፊነት፣ በራስ መተማመንና የእርስበርስ ማህበራዊ ግንኙነታቸውን ሊያዳብር እንደሚችል የመምህራንን ግንዛቤ ሊጨምር ይችላል።

### 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በቤንች ሸኮ ዞን ከሚገኙ 246 የመንግስት የመጀመሪያ ደረጃ(1-8) ትምህርት ቤቶች ውስጥ በወሸቅን ትምህርትቤት በሚማሩ የ5ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ብቻ የተገደበ ነው። ለጥናቱ የተመረጡ ምድቦችም ከሦስቱ ምድቦች "ሀ" እና"ለ" ብቻ ናቸው። በተጨማሪም ጥናቱ ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች ውስጥ በማንበብ ክሂል ላይ ብቻ አተኩሯል። ምክንያቱም የማንበብ ክሂል ትምህርት የሁለተኛ ቋንቋንም ሆነ የውጭ

ቋንቋን ለሚማሩ ተማሪዎች ከሌሎች ክሂሎች በተሻለ ሁኔታ ተማሪዎችን ለበርካታ አረፍተነገሮች ሰዋስዋዊ ሥርዓት እና ለአዳዲስ ቃላት የማጋለጥ ጠቀሜታ አለው(Dong, 2019)።

ከትምህርታዊ ጨዋታዎች ውስጥም በJesa, 2005; Wright et al., 2006 እውቅና ከተሰጣቸው በርካታ የሁለተኛ ቋንቋ የክፍል ውስጥ ማስተማሪያ ትምህርታዊ ጨዋታዎች (ለምሳሌ፤ የቃላት ጨዋታዎች፣ የግመታ ጨዋታዎች፣ የማዛመድ ጨዋታዎች፣ የኮምፒውተር ላይ ጨዋታዎች፣ የሞባይላ ላይ ጨዋታዎች፣ የቅደምተከተላዊ ጨዋታ፣ ወዘተ.) ውስጥ በቅደምተከተላዊ ጨዋታዎችላይ ብቻ የተወሰነ ነው። ምክንያቱም አጥኚው በዚህ ጨዋታ ተማሪዎች ያነበቡትን መልእክት ተገንዝበው የሃሳብ ቅደምተከተልን በማስተካከል ሂደት ውስጥ ከሌሎች ጨዋታዎች በተሻለ የተማሪዎችን ትኩረት በመያዝ የማንበብ ፍላጎታቸውን ይጨምራል ብሎ ስላሰበ ነው።

## 1.7 የቁልፍ ቃላትና ሀረጋት ፍቺ

### 1.7.1 የማንበብ ተነሳሽነት፡-

ተነሳሽነት ማለት ሰዎች አንድን ድርጊት ለማከናወን ወይም በአንድ ተግባር ለመሳተፍ የሚነሳሱበትና በዚህም የውድድር ስሜት የሚሰማቸው ሁኔታ ነው (Ecceles & Wigfield, 2002)። በዚህ ጥናት ውስጥም የተማሪዎችን ለማንበብ ያላቸውን ተነሳሽነት ይመለከታል።

### 1.7.2 ትምህርታዊ ጨዋታ

ትምህርታዊ ጨዋታ አንድን የትምህርት ዓይነት ወይም አንድን ክሂል ለሰዎች ለማስተማር ታስቦ የተቀረፀ ወይም የተዘጋጀ ጨዋታ ማለት ነው›› (King, 2011)። በዚህ ጥናት ውስጥም ለተማሪዎች የተዘጋጁትን የማንበብ ክሂል ይዘቶች በትምህርታዊ ጨዋታዎች አማካኝነት ማስተማርን ይመለከታል።

### 1.7.3 የተለመደው የማስተማሪያ ስልት

የተለመደውየማስተማርስልትየማንበብችሎታቸውየተሻሉተማሪዎችንብቻትኩረትያደረገየማንበብክሂልማስተ ማሪያስልትነው (Kawaguchi, 2010; Phajane, 2014)። በዚህ ጥናት ውስጥ ግን “የተለመደው የማስተማሪያ ስልት” የሚለው ሀረግ የማንበብ ክሂል ትምህርቱ ይዘቶች በመማሪያ መጽሀፉ በቀረቡባቸው መመሪያዎችና መልመጃዎች መሠረት ማስተማርን የሚመለከት ነው።

## 2. የጥናቱ ዘዴ፤

### 2.1 የጥናቱ ንድፍ

የዚህ ጥናት ዓላማ አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎችን የማንበብ ክሂል ትምህርት በትምህርታዊ ጨዋታ ስልት ማስተማር በማንበብ ተነሳሽነታቸው ላይ ያለውን ሚና መመርመር ነው። በመሆኑም ጥናቱ ፍትነት መሰል የምርምር ንድፍን ተግባራዊ ያደረገ ሲሆን አንድ የቁጥጥር ቡድን እና አንድ የሙከራ ቡድንን ይዟል። ይህ ንድፉ የተመረጠበት ምክንያትም ፍትነት መሰል የምርምር ንድፍ ዋና ዓላማው ተመራማሪው የሚጠቀመውን አዲስ የማስተማሪያ ስልት ውጤታማነት መገምገም ነው (Ary et al., 2010)። በተጨማሪም ጥናቱ ሁለት ነፃ ተለዋዋጮች(ትምህርታዊ ጨዋታ የማስተማር ስልትና የተለመደው የማስተማር ስልት) እንዲሁም አንድ ጥገኛ ተለዋዋጭን (የማንበብ ተነሳሽነትን) ያካተተ ነው።

### 2.2 የናሙና አመራረጥ

የጥናቱን ቦታ በሚመለከትአጥኚው በቤንች ሸኮ ዞን ከሚገኙ 246 የመንግሥት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትቤቶች ውስጥ የወሽቅን መጀመሪያ ደረጃ (ከ1ኛ-8ኛ ክፍል) ትምህርትቤትን በአመቺ የንሞና ስልት መርጧል። ምክንያቱም በዚህ ትምህርትቤት የሚማሩ ተማሪዎች የመኖሪያ አካባቢያቸውም ታላሚው ቋንቋ በስፋት ከሚነገርበት አካባቢ የራቀ በመሆኑና ሁሉም ተተኳሪ ተማሪዎች ከትምህርትቤት ውጭ ለቋንቋው የመጋለጥ እድላቸው በተመሳሳይ ሁኔታ አናሳ ይሆናል ተብሎ ስለታሰበ ነው። ተተኳሪ የክፍል ደረጃን ናሙና አመራረጥ በተመለከተም የ5ኛ ክፍል በዓላማተኮር የንሞና ስልት ተመርጧል። ምክንያቱም አጥኚው በዚህ ደረጃ ያሉ ተማሪዎች እድሜያቸው በትምህርታዊ ጨዋታዎች ለማስተማር ተመራጭ በመሆኑና ለማንበብ የሚማሩ (learn to read) ሳይሆኑ በማንበብ የሚማሩ (read to learn) ናቸው ብሎ ከማሰቡ የተነሳ የማንበብ ተነሳሽነታቸውን ደረጃ መፈተሽ ተገቢነው ብሎ ስላመነ ነው።

በአንፃሩ ከተመረጠው የክፍል ደረጃ በላይ የሚማሩትን ተማሪዎችን የጥናቱ አካል ቢደረጉ ከእድሜያቸው መጨመር ጋር ተያይዞ በትምህርታዊ ጨዋታዎች ማስተማር በእድሜ ዝቅተኛ እንደሆኑት ተማሪዎች በሚጠበቀው ልክ ውጤታማ ሊሆኑ እንደማይችሉ ምሁራን ያስረዳሉ። ለምሳሌ Yolageldili and Arikan (2011) (Rixon, 1999)ን ዋቢ በማድረግ በተለይም እድሜያቸው ከ5-12 ዓመት እድሜ የሆኑትን ተማሪዎች በትምህርታዊ ጨዋታዎች ማስተማር ከማዝናናቱና ነፃነት ከመስጠቱ በተጨማሪ ቋንቋውን ፈጠራዊ እንዲሁም ተግባቦታዊ በሆነ ሁኔታ እንዲማሩት የሚያበረታታ መሆኑን አመላክተዋል። በተመሳሳይ Nitiasih and Budiartha (2020) እንደገለጹት በተለይ ከ5-12 የእድሜ ክልል ላሉ ተማሪዎች የማንበብ ክሂሉን የትምህርት

ይዘት በትምህርታዊ ጨዋታዎች አስደግፎ ማቅረብ የማንበብ ተነሳሽነታቸው በእድሜ ከፍ ካሉት ተማሪዎች በተሻለ ሁኔታ ውጤታማ ያደርጋቸዋል፡፡

የጥናቱ ተሳታፊዎችን የናሙና አመራረጥ በተመለከተ በእየምድቡ የሚገኙ ተማሪዎች ብዛት ጥቂት የሚባል በመሆኑ አጥኚው የጠቅላይ ንሞናን ተጠቅሟል፡፡ በዚሁም መሠረት የሙከራ ቡድን 35፤ የቁጥጥር ቡድን 35 በአጠቃላይ ድምሩ 70 ተማሪዎችየጥናቱ አካል ተደርገዋል፡፡ የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች አማካይ እድሜም 11.77 ሲሆን የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ደግሞ 12.09 ሆኖ በመገኘቱ በሁለቱ ቡድን ተማሪዎች መካከል የእድሜ ተመጣጣኝነትመኖሩን ያመለክታል፡፡

ለተተኳሪ ተማሪዎች የተመረጡት መምህርም ለ5ኛ ክፍል ከተመደቡት ሁለት መምህራን ውስጥ አጥኚው በመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ምድቦች የሚያስተምሩትን መምህር በዓላማተኮር የንሞና ስልት መርጧል፡፡ ይህ የንሞና ስልት የተመረጠበት ምክንያትም አጥኚው ለሙከራ ቡድንና ለቁጥጥር ቡድን የሚፈለገውሁለት ምድቦችን ብቻ በመሆኑና ተማሪዎች በእንግዳ መምህር ከሚማሩ ይልቅ በለመዱት መምህር መማራቸው ሊፈጠርባቸው ከሚችል እንግዳዊ ስሜት ጋር ተዳምሮ በጥናቱ ውጤት ላይ ሊያስከትል ከሚችለው አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተጽእኖ ነፃ ለመሆን ያግዛል ከሚል መነሻነት ነው፡፡ ለተመረጡት መምህርም ስለአተገባበሩ በልምምድ የተደገፈ ስልጠና በአጥኚው ተሰጥቷቸዋል፡፡የምድብ መረጣን በተመለከተም አጥኚው በአመቺ የንሞና ስልት መርጧል፡፡ ምክንያቱም በአጠቃላይ በ2015 ዓ.ም በ5ኛ ክፍል ተማሪ እየተማረባቸው ያሉት ምድቦች ብዛት ሦስት ሲሆኑ ከእነዚህ ውስጥ ሁለቱ ምድቦች(ምድብ “ሀ” እና ምድብ “ለ ”) በአንድ መምህር የሚማሩ ሲሆኑ ቀሪው ምድብ “ሐ ” ደግሞ በሌላ የቋንቋው መምህር የሚማሩ ናቸው፡፡ በመሆኑም ምድብ “ሐ ” በእጣው ቢካተትና ቢመረጥ የመምህሩ እንግዳ መሆን በተማሪዎች ስነልቦናላይ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያስከትል ይችላል፡፡ ስለሆነም በአንድ መምህር የሚማሩትን ሁለት ምድቦች የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት በአመቺ የንሞና ስልት መርጧል፡፡

የትምህርቱን አሰጣጥ በተመለከተም የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች በመማሪያ መጽሀፉ የቀረቡትን የማንበብ ክሂል ይዘቶች በቀረቡባቸው መሠረት(መመሪያዎችና መልመጃዎች) የተማሩ ሲሆን፤ የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ደግሞ የመማሪያ መጽሀፉን የማንበብ ክሂል ይዘቶች ባገናዘበ ሁኔታ ቀደም ብሎ በአጥኚው እየተዘጋጁ በሚቀርቡ ካርዶችና ቁርጥራጭ ወረቀቶች ላይ በልዩ ልዩ ቀለማት እየተፃፉ የሚቀርቡ ጽሁፎችን በጥንድና በቡድን እየሆኑ በማንበብ የሃሳብ ቅደምተከተላቸውን በውድድር መንፈስ ፈጥኖ በማስተካከል የምንባቡን መልእክት ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡ በማድረግ ለ16 ሳምንታት ተከናውኗል፡፡

## 2.3. የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ

አጥኚው የጥናቱን መረጃዎች ለመሰብሰብ የቅድመና ድህረትምህርት የጽሁፍ መጠይቆችን ተጠቅሟል፡፡ እነዚህ የጽሁፍ መጠይቆች ለመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት ደረጃዎችን ለመለካት ያገለግላሉ ተብለው በ Guthrie and Wigfield (1997) ከተዘጋጁ 53 ጥያቄዎች ውስጥ ተማሪዎች ታላሚውን ቋንቋ መማር ከጀመሩበት የክፍል ደረጃ (3ኛ ክፍል)እና ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታዎች አንፃር ይመጥናሉ ያላቸውን 20 ጥያቄዎች በማላመድ (adaptation) ሳይሆን ቀጥተኛ የአማርኛ አቻ ትርጉማቸውን በመውሰድ ከሁለቱም ቡድኖች የማንበብ ተነሳሽነት ደረጃ መረጃዎችን ሰብስቧል፡፡ የጥያቄዎችን አስተማማኝነት በተመለከተም ጉዝሪ እና ዊግፊልድ በተለያዩ ትምህርትቤቶች ላይ ባደረጓቸው ፍተሻዎች የተገኘው የአስተማማኝነት ውጤት በ0.52 እና በ0.81 መካከል መሆኑን በመግለፃቸው አጥኚው አስተማማኝናቸው በማለት ተጠቅሞባቸዋል፡፡

የተመረጡት ጥያቄዎችም የማንበብ ብቃትን (**Reading Efficiency items**፡- I am a good reader) 1(5%)፣ አዳዲስ ጽሁፎችን የማንበብ ጉጉት (**Reading Curiosity items**፡- If the teacher discusses something interesting I might read more about it; I have favorite subjects that I like to read about; I read to learn new information about topics that interest me) 3(15%)፣ አዘውትረው የሚሳተፉባቸው ምንባቦች (**Reading Involvement Items**፡- I read stories about fantasy and make believe; I make pictures in my mind when I read; I read a lot of adventure stories) 3(15%)፣ ከንባብ የሚያርቁ ነገሮች (**Reading Work Avoidance Items**፡- Complicated stories are no fun to read; I don't like reading something when the words are too difficult) 2(10%)፣ የንባብ ውድድር (**Competition for Reading Items**፡- I try to get more answers right than my friends; I like being the best at reading; I like to finish my reading before other students; I like being the only one who knows an answer in something we read; It is important for me to see my name on a list of good readers) 5 (25%)፣ በንባብ እውቅናን ለማግኘት (**Recognition for Reading Items**፡- My parents often tell me what a good job I am doing in reading)1(5%)፣ ለውጤት ሲሉ ማንበብ (**Reading for Grades Items**፡- I read to improve my grades) 1(5%)፣ ለማህበራዊነት ሲባል ማንበብ (**Social Reasons for Reading Items**፡- I often read to my brother or my sister; I like to tell my family about what I am reading) 2(10%) እና አሟልቶ ማንበብ (**Compliance Reading Items**፡- I read because I have to; I always try to finish my reading on time) 2(10%)

የሚሸፍኑ ናቸው። የፐርሰንት ድልድሉን አጥኚው ለጥናቱ ዓላማ ተገቢ መረጃን ማስገኘት ይችላሉ ብሎ ያሰባቸውን በመምረጥ የተከናወነ ነው።

ጥያቄዎቹ ባለአራት አማራጮች ሲሆኑ እነሱም 1(በጣም አልስማማም) ፣ 2(አልስማማም)፣ 3(እስማማለሁ) እና 4(በጣም እስማማለሁ) የሚሉትን የመወሰኛ ደረጃዎችን (የሊከርት ስኬል) በመጠቀም የተተኳሪ ተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነት መለኪያነት ውለዋል። በዚህም መሠረት ጥያቄዎቹ ለተማሪዎች ቀርበው ከተሞሉ በኋላ በቅድመትምህርት መጠይቆች የተገኙ ውጤቶች ለቅድመ ትምህርቱ፤ በድህረ ትምህርቱ የተገኙት ደግሞ ለድህረ ትምህርቱ ውጤት በመሆን ተመዝግበዋል።

### 2.4 የመረጃ አተናተን

የጥናቱን የመረጃ አተናተንን በተመለከተአጥኚው የተተኳሪ ተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነት በሚመለከት የጽሁፍ መጠይቆችን በመጠቀም ከቅድመና ድህረትምህርት የተሰበሰቡ መረጃዎችን የነፃ ናሙና ቲ-ቴስት ስታትስቲካዊ የመተንተኛ ስልትን በመጠቀም ተንትኗል። ይህ ስታትስቲካዊ መተንተኛ ስልት የተመረጠበት ምክንያትም በሁለት የተለያዩ ነፃ ቡድኖች መካከል ጥገኛ ተለዋዋጮች በጊዜ ልዩነት ያሳዩት የአማካይ ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩ የሚወዳደርበት የትንተና ስልት ነው(Ullah, 2011)። በመሆኑም በሁለቱ ነፃ ተለዋዋጮች (የማስተማሪያ ስልቶች) ከጥገኛ ተለዋዋጩ (ከማንበብ ተነሳሽነት አንፃር) የተገኙ የቅድመና ድህረ ትምህርት የተነሳሽነት መለኪያ ውጤቶች መካከል ያለውን ግንኙነት(ተዛምዶ) በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ቀመር በመታገዝ፤ እንዲሁም በቡድኖቹ መካከል ያለውን የአማካይ፣ መደበኛ ልይይትና የጉልህነት ደረጃቸውን በማስላት የጥናቱን መሠረታዊ ጥያቄዎችና መላምቱን ተመርኩዞው እንደሚከተለው ተተንትነዋል፡
:

## 3. የመረጃ ትንተና

**3.1** በዚህ ጥናት የመጀመሪያው የምርምር ጥያቄ«**አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎችን የማንበብ ክሂል ትምህርት በትምህርታዊ ጨዋታ ስልት ማስተማር ከተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት ጋር ከተለመደው ስልት የተለየ ግንኙነት አለውን?** » የሚል ሲሆን፤ መላምቱ ደግሞ በሁለቱ የማስተማር ስልቶች መካከል የተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነት ከማዳበር አኳያ የተለየ ግንኙነት የለም የሚል ነበር።

ሠንጠረዥ 1
የቅድመትምህርቱ የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖች የተነሳሽነት ተዛምዶ በፒርሰን የተዛምዶ መለኪያ ቀመር

**Correlations**

| | | group | motivation_score1 |
|---|---|---|---|
| group | Pearson Correlation | 1 | .067 |
| | Sig. (2-tailed) | | .581 |
| | N | 70 | 70 |
| motivation_score1 | Pearson Correlation | .067 | 1 |
| | Sig. (2-tailed) | .581 | |
| | N | 70 | 70 |

ከላይ በሠንጠረዥ 1 እንደተመለከተው ከጽሁፍ መጠይቁ የተገኘው በሁለቱ ቡድኖች መካከል ያለው የቅድመ ትምህርት የማንበብ ተነሳሽነት ተዛምዶ በፒርሰን የተዛምዶ መለኪያ ቀመር r= .067 ሆኗል። ይህም ከዜሮ በላይ (r=> 0) በመሆኑ በሁለቱ የማስተማሪያ ስልቶች (ቡድኖች) መካከል አዎንታዊ ግንኙነት (ልዩነት የለም) ማለት ነው። በሌላ አገላለጽ የአዎንታዊ ግንኙነት ደረጃው ደካማ ሊባል የሚችል ቢሆንም በተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት ላይ ተመሳሳይ ሚና እንዳላቸው አንዱ ሲጨምር ሌላውም አብሮ እንደሚጨምር አሳይቷል። በተመሳሳይ የጥናቱን መላምትም የደገፈ ሆኖ ተገኝቷል።

ሠንጠረዝ 2
የድህረ ትምህርቱ የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖች የተነሳሽነት ተዛምዶ በፒርሰን የተዛምዶ መለኪያ ቀመር

**Correlations**

| | | group | motivation_score2 |
|---|---|---|---|
| group | Pearson Correlation | 1 | -.306* |
| | Sig. (2-tailed) | | .010 |
| | N | 70 | 70 |
| motivation_score2 | Pearson Correlation | -.306* | 1 |
| | Sig. (2-tailed) | .010 | |
| | N | 70 | 70 |

*. Correlation is significant at the 0.05 level (2-tailed).

ከላይ በሠንጠረዥ 2 ማየት እንደሚቻለው በድህረትምህርቱ በሁለቱ ቡድኖች መካከል የተገኘው የተዛምዶ መጠን r= -.306 ሆኗል። ይህም ውጤት ከዜሮ በታች(r=<0) በመሆኑ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ከቅድመትምህርቱ ይልቅ በድህረትምህርቱ አሉታዊ ግንኙነት ታይቶባቸዋል። ይህም በሁለቱ ቡድኖች መካከል ልዩነት መኖሩን ያሳያል።

በአጠቃላይ በሁለቱ የማንበብ ክሂል ማስተማሪያ ስልቶች መካከል ምንም እንኳ በቅድመ ትምህርቱ የነበራቸው ተዛምዶ አዎንታዊ የነበረ ቢሆንም በድህረ ትምህርቱ የታየው ግን በሁለቱ የማስተማሪያ ስልቶች መካከል አሉታዊ ግንኙነት ወይም ተዛምዶ መኖሩን አመላክቷል።

3.2 የዚህ ጥናት ሁለተኛ ጥያቄ የነበረው “ **አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎችን የማንበብ ክሂል ትምህርት በትምህርታዊ ጨዋታ ስልት ማስተማር በተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነት ደረጃ ላይ በተለመደው ስልት ከማስተማር የተለየ ጉልህ ልዩነት አለውን?** ” የሚል ሲሆን፤ መላምቱ ደግሞ በሁለቱ የማስተማሪያ ስልቶች መካከል የተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነት በማሳደግ ረገድ ጉልህ ልዩነት የለም የሚል ነበር። በዚሁም መሠረት አጥኚው በሁለቱ ቡድኖች መካከል ያለውን የአማካይ፣ መደበኛ ልይይትና የጉልህነት መጠናቸውን በነፃ ናሙና ስታትስቲካዊ ስልት በመታገዝ እንደሚከተለው ተንትኗል።

<u>ሠንጠረዥ 3</u>

የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖች የቅድመ ትምህርት የማንበብ ተነሳሽነት የአማካይና የመደበኛ ልይይት መጠን

| ቡድን | የናሙና ብዛት | አማካይ | መደበኛ ልይይት | መደበኛ ስህተት |
|---|---|---|---|---|
| የሙከራ ቡድን | 35 | 50.54 | 5.409 | .914 |
| የቁጥጥር ቡድን | 35 | 51.29 | 5.798 | .980 |

በሠንጠረዡ 3 እንደሚታየው የጽሁፍ መጠይቅ የተገኘው የቁጥጥር ቡድኑ አማካይ ውጤት (M= 51.29) ሲሆን የሙከራ ቡድኑ አማካይ (M= 50.54) ሆኗል። በሌላ በኩል መደበኛ የልይይት መጠናቸውን በሚመለከት ከቁጥጥር ቡድኑ የተገኘው ልይይት (SD= 5.798) ሲሆን የሙከራ ቡድኑ ደግሞ (SD= 5.409) ሆኖ ተገኝቷል። ይህም የሁለቱ ቡድኖች የቅድመትምህርት የማንበብ ተነሳሽነት ውጤት ተቀራራቢ መሆኑን ያመላክታል። ይሁንእንጅ በቡድኖች መካከል የተገኙትን የአማካይና የልይይት መጠን ብቻ በማየት በመካከላቸው ያለውን የተዛምዶ መጠን መወሰን አንችልም። ስለሆነም ስታትስቲካዊ ስሌቱ የሚያሳየውን የነፃነት ደረጃና የጉልህነት ደረጃ ማየት ተገቢ ይሆናል።

<u>ሠንጠረዥ 4</u>

የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖች የቅድመ ትምህርት የማንበብ ልዩነት የጉልህነት ደረጃ

| ቡድን | የሊቬን እኩል ልይይት ሙከራ | የቲ-ቴስት እኩልነት አማካይ | |
|---|---|---|---|
| | የነፃነት ደረጃ | የጉልህነት ደረጃ | የመደበኛ ስህተት ልዩነት |
| የሙከራ ቡድን<br>የቁጥጥር ቡድን | .301 | .581<br>.581 | 1.340<br>1.340 |

ከላይ ሠንጠረዥ ‹‹ 4›› ሥር በቀረበው መሠረት በቡድኖቹ መካከል የተገኘው የነፃነት ደረጃና የጉልህነት ደረጃ (*F*= 0.301; *P*= 0.581) ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለዚህም ከሁለቱ ቡድኖች የቅድመትምህርት የጽሁፍ መጠይቁ ስታትስቲካዊ ስሌት ውጤት የተገኘው የጉልህነት መጠን ከ0.05 በላይ በመሆኑ የማንበብ ክሂልን በተለመደው ስልት በማስተማርና በትምህርታዊ ጨዋታ ስልት በማስተማር መካከል በተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት ላይ ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ጥናቱ አመላክቷል፡፡ በተመሳሳይ ጥናቱ ይዞት የተነሳውን በቡድኖች መካከል ጉልህ ልዩነት የለም የሚለውን መላምትም የጥናቱ ውጤት ደግፎታል፡፡

<u>ሠንጠረዥ 5</u>

የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖች የድህረ ትምህርት የማንበብ ተነሳሽነት የአማካይና የመደበኛ ልይይት መጠን

| ቡድን | የናሙና ብዛት | አማካይ | መደበኛ ልይይት | መደበኛ ስህተት |
|---|---|---|---|---|
| የሙከራ ቡድን 1 | 35 | 55.06 | 4.640 | .784 |
| የቁጥጥር ቡድን 1 | 35 | 51.77 | 5.688 | .962 |

ከላይ በሠንጠረዥ ‹‹5›› የቀረበው ውጤት የሚያሳየውን አማካይ ውጤት ስንመለከት የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች አማካይ ውጤት (M= 51.77) ሲሆን የሙከራ ቡድኑ ደግሞ (M= 55.06) ሆኗል፡፡ በተጨማሪም በቡድኖቹ የታየው የመደበኛ ልይይት መጠን የቁጥጥር ቡድኑ (SD= 5.688) ሲሆን የሙከራ ቡድኑ ደግሞ (SD= 4.640) ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም በሁለቱ ቡድኖች መካከል የድህረ ትምህርት የማንበብ ተነሳሽነት የአማካይ ውጤትና የልይይት መጠን ላይ መጠነኛ ልዩነት መኖሩን ያሳያል፡፡


<u>ሠንጠረዥ 6</u>

የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖች የድህረ ትምህርት የማንበብ ልዩነት የጉልህነት ደረጃ

| ቡድን | የሊቬንእኩል ልይይት ሙከራ | የቲ-ቴስት እኩልነት አማካይ | |
|---|---|---|---|
| | የነፃነት ደረጃ | የጉልህነት ደረጃ | የመደበኛ ስህተት ልዩነት |
| የሙከራ ቡድን | 1.353 | .010 | 1.241 |
| የቁጥጥር ቡድን | | .010 | 1.241 |

ከላይ በሠንጠረዥ ‹‹ 6 ›› ሥር እንደቀረበው በሁለቱ ቡድኖች መካከል ያለው ጉልህነት (*F*= 1.353; *P*= 0.010) መሆኑን ጥናቱ አመላክቷል፡፡ ይህም የተገኘው የጉልህነት መጠን ከ0.05 በጣም ያነሰ በመሆኑ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ማለትም የማንበብ ክሂልን በተለመደው የማስተማሪያ ስልት በማስተማርና በትምህርታዊ ጨዋታ ስልት በማስተማር መካከል የተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት ደረጃ ጉልህ ልዩነት አሳይቷል ማለት ነው፡፡

በተጨማሪም ‹‹በሁለቱ የማስተማሪያ ስልቶች መካከል በተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት ላይ ጉልህ ልዩነት የለም›› የሚለውን መላምት ውድቅ አድርጓል፡፡




ግራፍ 1

የቁጥጥሩና የሙከራ ቡድኑ ቅድመትና ድህረ ምህርት የማንበብ ተነሳሽነት ደረጃ የውጤት ስርጭት በባለመስመር ግራፍ ሲታይ

ግራፍ አንድ ላይ ማየት እንደሚቻለው የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች በቅድመ ትምህርት የተገኘው የማንበብ ተነሳሽነት ደረጃቸው ከሙከራ ቡድኑ የተሻለ ነው፡፡ በድህረ ትምህርት ውጤታቸውም መጠነኛ የማንበብ ተነሳሽነት እንዳሳዩ ግራፉ ያሳያል፡፡ ነገር ግን የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ምንም እንኳ በቅድመ ትምህርት ወቅት ያስመዘገቡት የማንበብ ተነሳሽነት ደረጃ ውጤት ከቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ያነሰ ቢሆንም በድህረ ትምህርቱ ግን በተቃራኒው ከቁጥጥር ቡድኑ በጣም ከፍ ባለ ሁኔታ የማንበብ ተነሳሽነት ደረጃ ታይቶባቸዋል፡፡

## 4. የጥናቱ ውጤት

የዚህ ጥናት ዓላማ በ2015 ዓ.ም አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ በወሽቅን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትቤት የ5ኛ ክፍል ተማሪዎችን የማንበብ ክሂል ትምህርት በትምህርታዊ ጨዋታ ስልት ማስተማር በተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት ላይ ከተለመደው የማስተማር ስልት የተለየ ጉልህ ሚና ያለው መሆን አለመሆኑን ለመመርመር የተደረገ ጥናት ነው፡፡ በተጨማሪም ጥናቱ የተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነት

ከመጨመር አኳያ በሁለቱ የማስተማሪያ ስልቶች መካከል ግንኙነትም ሆነ የጎላ ልዩነት የለም የሚሉ ሁለት መላምቶችን ፈትሿል።

በዚሁም መሠረት የጥናቱ የመጀመሪያ ጥያቄ "**አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎችን የማንበብ ክሂል ትምህርት በትምህርታዊ ጨዋታ ስልት ማስተማር ከተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት ጋር ከተለመደው ስልት የተለየ ግንኙነት አለውን?**" የሚል ሲሆን፤ መላምቱ ደግሞ በሁለቱ የማስተማር ስልቶች መካከል የተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነት ከማዳበር አኳያ የተለየ ግንኙነት የለም የሚል ነበር። በመሆኑም በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ቀመር መሰረት በቅድመትምህርቱ በሁለቱ የማስተማሪያ ስልቶች (ቡድኖች) መካከል የአዎንታዊ ግንኙነት ደረጃው ደካማ ሊባል የሚችል ቢሆንም በተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት ላይ ተመሳሳይ ሚና እንዳላቸው አሳይቷል። በተመሳሳይ የጥናቱን መላምትም የደገፈ ሆኖ ተገኝቷል። በአንፃሩ በድህረትምህርቱ የተገኘው የተዛምዶ ውጤት የተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነት በማዳበር ረገድ በሁለቱ የማስተማሪያ ስልቶች መካከል ልዩነት መኖሩን አሳይቷል። በተመሳሳይ ጥናቱ ይዞት የተነሳውን በሁለቱ የማስተማሪያ ስልቶች መካከል የማንበብ ተነሳሽነትን ከማዳበር አኳያ ግንኙነት የለም የሚለውን መላምት ውድቅ ያደረገ ሆኗል።

የዚህ ጥናት ሁለተኛ ጥያቄ የነበረው " **አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎችን የማንበብ ክሂል ትምህርት በትምህርታዊ ጨዋታ ስልት ማስተማር በተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት ደረጃ ላይ በተለመደው ስልት ከማስተማር የተለየ ጉልህ ልዩነት አለውን?**" የሚል ሲሆን፤ መላምቱ ደግሞ በሁለቱ የማስተማሪያ ስልቶች መካከል የተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነት በማሳደግ ረገድ ጉልህ ልዩነት የለም የሚል ነበር።በዚሁ መሠረትም በቅድመትምህርቱ በሁለቱ ቡድኖች መካከል የተገኘው የጉልህነት ውጤት ከ0.05 በላይ በመሆኑ የተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነት ከማዳበር አንፃር በሁለቱ ማስተማሪያ ስልቶች መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ጥናቱ በማመላከቱ ይዞት የተነሳውን መላምት የደገፈ ሆኗል። በተቃራኒው በድህረትምህርቱ በሁለቱ ቡድኖች መካከል የተገኘው የጉልህነት መጠን ከ0.05 በጣም ያነሰ በመሆኑ በሁለቱ የማስተማሪያ ስልቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን በማመላከቱ የጥናቱን መላምት ውድቅ ያደረገ ሆኗል። በተጨማሪም ከቅድመትምህርቱ ይልቅ በድህረትምህርቱ የሁለቱ ቡድኖች የአማካይ ውጤት ሲነፃፀር የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ከቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች የበለጠ ከፍተኛ ውጤት አሳይተዋል። ከባለመስመር ግራፉም ይህንኑን የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ውጤት የተሻለ መሆኑን ማስተዋል ተችሏል። በመሆኑም ለተማሪዎች የማንበብ

ተነሳሽነት መጨመር ከተለመደው የማንበብ ክሂል ማስተማሪያ ስልት ይልቅ የትምህርታዊ ጨዋታው ስልት የተሻለ መሆኑን የጥናቱ ውጤት አመላክቷል።

## 5. ውይይት (Discussion)

ይህ ጥናት በቤንች ሸኮ ዞን በወሽቅን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2015 ዓ.ም አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የተማሩ የ5ኛ ክፍል ተማሪዎችን የማንበብ ክሂል ትምህርት በትምህርታዊ ጨዋታ ስልት ማስተማር በተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት ላይ ከተለመደው ስልት በተለየ ያለውን ሚና መመርመርን ዓላማ ያደረገ ነበር። በዚህም በቅድመ ትምህርቱ የመጀመሪያው የጥናቱ ጥያቄ የማንበብ ተነሳሽነት ከትምህርታዊ ጨዋታ ጋር ግንኙነት የለውም የሚል መላምትን ፈትሿል። በተገኘው ውጤትም በቅድመ ትምህርቱ በሁለቱ ቡድኖች መካከል በፒርሰን የተዛምዶ መጠን መለኪያ ቀመር የተገኘው ውጤት ከዜሮ በላይ በመሆኑ በሁለቱ ቡድኖች (በሁለቱ የማስተማሪያ ስልቶች) መካከል ግንኙነት አለመኖሩን (ግንኙነቱ አዎንታዊ መሆኑን) በማመላከቱ መላምቱን የደገፈ ውጤት ታይቷል። በተመሳሳይ በነፃ የናሙና ቲ-ቴስት ስታትስቲካዊ ስሌት በሁለቱ ቡድኖች መካከል የተገኘው የጉልህነት መጠን ከ.05 በላይ በመሆኑ በመካከላቸው ጉልህ ልዩነት አለመኖሩንና መላምቱንም መደገፉን አሳይቷል። ይህም የጥናት ውጤት የተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነት ማዳበር የሚቻለው የማስተማሪያ ስልትን በመቀያየር ሳይሆን በራሳቸው በተማሪዎች ፍላጎትና ውሳኔ ላይ የተመሠረተ ነው የሚል ሃሳብ ከሚያራምዱት የGuthrie et al., (2006) የGuthrie and Wigfield (2000) Wang and Guthrie (2004) እንዲሁም Deci (2001) ሃሳብ ጋር ተማሳሳይነት ታይቶበታል።

በአንፃሩ በድህረትምህርቱ የተገኘው የተዛምዶ መጠን ከዜሮ በታች በመሆኑ በሁለቱ የማስተማሪያ ስልቶች መካከል አሉታዊ ተዛምዶ መኖሩንና መላምቱንም ውድቅ ያደረገ ሆኗል። የድህረትምህርቱ የጽሁፍ መጠይቅ ውጤት በነፃ ናሙና ቲ-ቴስት ስታትስቲካዊ ስሌት ተሰልቶ የተገኘው የጉልህነት መጠን ከ.05 በታች በመሆኑ በሁለቱ የማስተማሪያ ስልቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን አሳይቷል። በተመሳሳይ በሁለቱ የማስተማሪያ ስልቶች መካከል ጉልህ ልዩነት የለም ብሎ የተነሳውን የጥናቱ መላምት ውድቅ አድርጓል። በጥናቱ ትንተና እንደተመለከተው የድህረትምህርቱ በሁለቱ ቡድኖች መካከል የተገኘው የማንበብ ተነሳሽነት አማካይ ውጤት ከቁጥጥሩ ይልቅ የሙከራ ቡድኑ ከፍ ብሎ በመታየቱ ትምህርታዊ ጨዋታ ከተለመደው የማስተማር ስልት የተሻለ መሆኑን አመላክቷል። ይህም ውጤት በGuthrie et al., (2007) ከተገለጸው እና ሻናሀን (2019)

(ካርትራይት እና ሌሎች፣ 2016)ን ጠቅሰው ትምህርታዊ ጨዋታዎች የማንበብ ተነሳሽነትን ለማዳበር አስፈላጊ ናቸው በማለት ከገለጹት ሃሳብ ጋር ተመሳሳይነት ታይቶበታል።

በሌላ በኩል ለተማሪዎች የሁለተኛ ቋንቋ የማንበብ ተነሳሽነት መዳበር የተለያዩ መንስዔዎች መኖራቸውን ምሁራን ንድፈሃሳባዊ እይታቸውን ሠንዝረዋል። ለአብነትምለማንበብ ተነሳሽነት መዳበር እንደምክንያት የሚነሱ ነጥቦችን በተመለከተ (Bandura, 1977) የማንበብ ተነሳሽነትን ለመፍጠር ግለሰባዊ ብቃት ሲኖር ለተለያዩ ክሂሎች መዳበርና ወደ ትግበራ ለመግባት ዋናው መስፈንጠሪያ ኃይል ነው። ለዚህ ኃይል መዳበርና ስኬታማነት ደግሞ የተማሪዎች ፈቃደኝነትና ጥረት መዳበር ትልቁን ድርሻ ይይዛል በማለት ገልጸዋል። የልጆች የማንበብ ተነሳሽነት ከሁለተኛ ቋንቋ መማር ጋር አዎንታዊ ቁርኝት ያለው መሆኑ ባያጠራጥርም ይህ የማንበብ ተነሳሽነት የሚወሰነው ግን ለሚማሩት ታላሚ ቋንቋ፣ ለቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ፣ ለቋንቋው ባለቤት የእርስ በእርስ ግንኙነት ሁኔታ ባላቸው አመለካከት ላይ ይወሰናል (Belmechri & Hummel,1998)። ከፍተኛ ውስጣዊ ተነሳሽነት ያለው ተማሪ ከፍተኛ የሆነ የመማር ፍላጎት እና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ይኖረዋል (Wigfield et al., 2006)።

በአንፃሩ በትምህርታዊ ጨዋታ ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ፍላጎት ከተለመደው ስልት በተሻለ እንደሚያዳብር Guthrie et al., (2007) ሲገልጹ፤ ሻናሀን (2019) (ካርትራይት እና ሌሎች፣ 2016)ን ዋቢ አድርገው ከጉዝሪ እና ሌሎች(2007) ጋር ተመሳሳይ ሃሳብ እንደሚያራምዱ ገልጸዋል። በሌላ ወገን ደግሞ Guthrie et al., (2006) Guthrie and Wigfield (2000) Wang and Guthrie (2004) Deci(2001) የማንበብ ተነሳሽነት ትምህርታዊ ጨዋታዎችንም ሆነ ሌሎች የማስተማሪያ ስልቶችን በመቀያየር አይመጣም፤ ይልቁንም ራሳቸው ተማሪዎቹ ለሚያነቡት ጽሁፍ በሚሰጡት የጊዜ፣ የትኩረት፣ የመስዕዋትነት፣ በአጠቃላይም በእነሱ ፍላጎትና አመለካከት ተጽእኖ ሥር ነው የሚል እይታ አላቸው። በኢትዮጵያ አውድ ያለውን ስንመለከት ግን አጥኚው ባደረገው የክለሳ ድርሳናት ፍተሻ የሁለተኛ ቋንቋን የማንበብ ክሂል በትምህርታዊ ጨዋታዎች ስልት ማስተማርን በተመለከተ የተደረገ ጥናት ባያጋጥመውም ባለው መረጃ ጥናቱን ባካሄደበት ዞን ያሉ አብዛኛዎቹ የመንግሥት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ በተግባር የሚታየው ሃቅ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ በየጊዜው እየታተሙ የሚቀርቡ የመማሪያ መጽሀፍትን የአንብቦ መረዳት መልመጃዎችና መመሪያዎች መሰረት ያደረገ መሆኑን ለመታዘብ ችሏል። በመሆኑም የተማሪዎችን የማንበብ

ተነሳሽነት ከማዳበር አንፃር አጥኚው እነዚህ አከራካሪ ሃሳቦች ተጨማሪ ጥናት ሊደረግባቸው ቢችል የሚል እይታ አለው፡፡

## 6.ማጠቃለያና የመፍትሄ ሃሳቦች

### 6.1 ማጠቃለያ

ከዚህ ጥናት ውጤት መረዳት እንደሚቻለው በሁለቱ ቡድኖች መካከል የተገኘው የቅድመትምህርቱ የተዛምዶ መጠን አዎንታዊ መሆኑንና መላምቱንም የደገፈ ሆኗል፡፡ ነገር ግን በድህረ ትምህርቱ ውጤት መሠረት በሁለቱ ቡድኖች መካከል አሉታዊ ተዛምዶ በመገኘቱ መላምቱንም ውድቅ አድርጎታል፡፡ በተመሳሳይ የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ምንም እንኳ በቅድመ ትምህርት ካስመዘገቡት የማንበብ ተነሳሽነት አማካይ ውጤት ይልቅ በድህረ ትምህርቱ ያስመዘገቡት በመጠኑ መሻሻልን ያሳየ ቢሆንም የድህረ ትምህርቱ አማካይ ውጤታቸው ግን ከሙከራ ቡድኑ አማካይ ውጤት ጋር ሲነፃፀር ያነሰ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በቅድመ ትምህርቱ በሁለቱ ቡድኖች መካከል የተገኘው የጉልህነት መጠን ከ.05 በላይ በመሆኑ በሁለቱ ቡድኖች የማንበብ ተነሳሽነት ደረጃ ላይ ጉልህ ልዩነት የለውም» የሚለውን የጥናቱን መላምት ደግፎ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በድህረ ትምህርቱ የተገኘው የጉልህነት መጠን ከ.05 በታች በመሆኑና ጉልህ ልዩነት በማሳየቱ መላምቱን ውድቅ ያደረገ ሆኗል፡፡ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ከነፃ ናሙና ስታትስቲካዊ ስሌቱ በተገኘው ውጤት መሠረትም በድህረ ትምህርቱ የሙከራ ቡድኑ አማካይ ውጤት ከቁጥጥር ቡድኑ አማካይ ውጤት የተሻለ መሆኑን ጥናቱ በማመላከቱ የማንበብ ክሂል ትምህርትን በተለመደው ስልት ከማስተማር ይልቅ በትምህርታዊ ጨዋታ ስልት ማስተማር የተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነት ደረጃ የበለጠ እንደሚጨምር አሳይቷል፡፡

### 6.2 የመፍትሄ ሃሳቦች

አጥኚው ከጥናቱ ውጤትና ማጠቃለያ በመነሳት የሚከተሉትን የመፍትሄ ሃሳቦች አቅርቧል፡፡

1. አማርኛ ቋንቋን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎችን የማንበብ ክሂል ትምህርት በትምህርታዊ ጨዋታ ስልት ማስተማር ለተማሪዎቹ የማንበብ ተነሳሽነት ደረጃ መዳበር ከተለመደው ስልት በተሻለ ሁኔታ አዎንታዊ ሚና እንዳለው የጥናቱ ውጤት አመላክቷል፡፡ ስለሆነም በኢትዮጵያ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራን የስልቱን ጠቀሜታ

ተገንዝበው ስለትምህርታዊ ጨዋታ የማንበብ ክሂል ማስተማሪያነት ያላቸውን ግንዛቤ በማዳበር የተማሪዎቻቸውን የማንበብ ተነሳሽነት ለማሻሻል ጥረት ቢያደርጉ፣

2. በኢትዮጵያ ትምህርት ሚኒስቴር በኩል ስለትምህርታዊ ጨዋታዎች የሁለተኛ ቋንቋ የማንበብን ክሂል ትምህርት ማስተማሪያነት ስለሚኖራቸው ሚና ተጨማሪ ጥናቶች እንዲካሄዱ በማድረግ ምን አልባትም ተመሳሳይ አዎንታዊ ውጤት የሚገኝ ከሆነ ስልቱን በሥርዓተ ትምህርቱ እንዲካተት በማድረግ የተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነት ለማዳበር ጥረት ቢደረግ፣

## ዋቢ ጽሁፎች


Aldabbus, S. (2008). An investigation into the impact of language games on classroom interaction and pupil learning in Libyan EFL primary classrooms (Doctoral dissertation, Newcastle University).

Akyol, H. (2011). Türkçe ilk okuma yazma öğretimi. (10. Baskı). Ankara: Pegmen Academy.

Ary, D., Jacobs, L. C. and Sorensen, C. (2010). Introduction to Research in Education(8th ed.). Printed in Canada.

Baker, L. & Wigfield A. (1999). Dimensions of children's motivation for reading and their relations to reading activity and reading achievement. Reading Research Quarterly, 34, ss. 1-45.

Bandura, A. (1977). Self- efficacy: Toward a Unifying theory of behavioral Change. Psychological Review.84, 191- 125.

Belmechri, F., & Hummel, K. (1998). Orientations and motivation in the acquisition of English as a second language among high school students in Quebec City. Language learning, 48(2), 219-244.

Boctor, L. (2013). Active-learning strategies: The use of a game to reinforce learning in nursing education. \A Case Study. Nurse education in practice13(2), 96-100. https://doi.org/10.1016/j.nepr.2012.07.01

Deci, E. L. (1971). Effects of externally mediated rewards on intrinsic motivation. Journal of Personality and Social Psychology, 18, 105–115. doi:10.1037/h0030644

Deci, E. L., Koestner, R., & Ryan, R. M. (2001). Extrinsic rewards and Intrinsic motivation in education: Revisited once again. Review of Educational Research, 1(27), 1-27. https://doi.org/10.3102/00346543071001001

Demirel, Ö. (2003). Türkçe ve sınıf öğretmenleri için Türkçe öğretimi.(5. Baskı). Ankara: Pegem AYayıncılık.

Fredricks, J. A., Blumenfeld, P. C., & Paris, A. H. (2004). School engagement: Potential of the concept, state of the evidence. Review of Educational Research, 74, 59–109. doi:10.3102/00346543074001059

Gardner, R., & Lambert, W. (1972). Attitudes and Motivation in Second Language learning. Rowley, MA: Newbury House Publishers.

Grabe W. (2009). Reading in second language: Moving from Theory to Practice. Northern Arizona University, Cambridge University Press.

Grabe, W. and Stoller, F. (2011). Teaching and Research Reading. Routledge.

Güneş, M. (1997). İlkokul öğrencilerinin okuma düzeyleri ve dikkat özelliklerinin bazı değişkenler açısından incelenmesi.Yayınlanmamış yüksek lisans tezi, Gazi Üniversitesi, Ankara.

Guthrie, J. T., Hoa, A. L. W., Wigfield, A., Tonks, S. M., Humenick, N. M., Littles, E. (2007). Reading Motivation and Reading Comprehension Growth in the later elementary years. Contemporary Educational Psychology 32 - 282 – 313. www.elsevier.com/locate/cedpsych.

Guthrie, J.T.& Wigfield, A. (1997). Relations of children's motivation for reading to the amount and breadth of their reading. Journal of Educational Psychology, 89, 420-432

Guthrie, J. T., & Wigfield, A. (2000). Engagement and motivation in reading. In M. L. Kamil, P. B. Mosenthal, P. D. Pearson, & R. Barr (Eds.), Handbook of reading research (Vol. 3, pp. 403–422). Mahwah, NJ: Erlbaum.

Guthrie J. T., Hoa L. W., Wigfield A., Tonks S. M., Perencevich K. C. (2006). From spark to fire: Can situationally reading interest lead to long-term reading motivation? Reading Research and Instruction, 45, 91–117.https://doi.org/10.1080/19388070609558444

Hariri, R. (2014). Educational Games and Their Implications for Children's Learning, 1st ed.; Dar Al- Yazuri Scientific for Publishing and Distribution: Amman, Jordan,

Jesa, M. (2005). Efficient English Teaching. New Delhi; A.P.H Publishing.

Kawaguchi, Janet. (2010). Improving Reading Comprehension: Traditional Reading Instruction VS Guided Reading Instruction in the case of Grade 2 Students Van cover. Island University MA thesis.

King, Nico. (2011). What are Educational Games? .https://www.chaostheorygames. com/blog/what-are-educational-games

Krashen, S. (1982). Principles and Practices in Second Language Acquisition. Pergamon Press Inc. https://bit.ly/35 NFIYT.

Maduku, T.; Zirawaga.V.S ; Olusanya, A. I. (2017). Gaming in Education: Using games as a support Tools to Teach History. Journal of Education and Practice. Vol. 8, No 15

Namaziandost, E., Churi, P., Asad, M. M., Palpanadan, S. T., & Ali, Z. (2022). Reading approaches Practiced in EFL Classrooms:

A Narative Review and Research Agenda. Asian Pacific Journal of Second and Foreign Language Education. Vol. 7, No. 28.

Nitiasih, P. K. & Budiartha, L. G. R. (2020). Increasing Students' Reading Comprehension Through Gamification Based on Balinese Local Stories. Advances in Social Science, Education and Humanities Research, volume 566. Atlantis Press.

Phajane, M. H. (2014). Traditional Method of Teaching Reading. Mediterranean Journal of Social Sciences MCSER Publishing. Rome-Italy.Vl.5,No. 15

Shanahan, Timothy. (2019). Improving Reading Comprehension in the Primary Class. Chicago: National Council for Curriculum and Assessment.

Taghizadeh, M., Vaezi, S., & Ravan, M. (2017). Digital Games, Songs and Flashcards and their Effects on Vocabulary Knowledge of Iranian Preschoolers. Studies, 5(4), 156-171.

Ullah, M. I. (2011). Independent Sample T-test Using SPSS. https://itfeature.com/testing-of-hypothesis/independent-sample-t-test-using-spss

Wang, Yong. (2018). Strategy Study on Primary School English Game Teaching. China Atlantic Press.

Wang, J. H. & Guthrie, J. T. (2004). Modeling the effects of intrinsic motivation, extrinsic motivation, amount of reading, and Past Reading achievement on text comprehension between U.S. and Chinese students. Reading Research Quarterly, 39(2), 162-186. https://doi.org/10.1598/RRQ.39.2.2.

Wigfield, A., Eccles, J. S., Schiefele, U., Roeser, R. W., & Davis-Kean, P. (2006). Development of achievement motivation. In W. Damon & R. M. Lerner (Eds.), Handbook of child psychology (Vol. 3, 6th ed., pp. 933–1002). New York, NY: Wiley.

Wright, A.; Betteridge, D. & Buckby, M. (2006). Games for Language Learning (3rd ed.). Cambridge: Cambridge University Press.

Yolageldili, G. and Arikan, A. (2011). Effectivness of using Games in Teaching Grammar to Young Learners. Elementary Education Online, 10 (1) 219-229.

Yu, Z.; Gao, M.; Wang, L. (2021**).** The effect of educational games on learning outcomes, student motivation, engagement and satisfaction. J. Educ. Compute. Res.59, 522–546.

# አባሪዎች

**አባሪ ሀ፡-** የተተኳሪ ተማሪዎችን የቅድመና ድህረ ትምህርት የማንበብ ተነሳሽነት ለመለካት እንደምንጭ ሆኖ አገልግሎት ላይ የዋለው የጽሁፍ መጠይቅ የእንግሊዝኛው ቅጂ

(የተቀለሙት ለዚህ ጥናት አገልግሎት ላይ የዋሉት ናቸው)

Motivations for Reading Questionnaire (MRQ)
Wigfield & Guthrie, 1997

53 items

11 constructs

**Reading Efficacy (3 items)**
- I don't know that I will do well in reading next year
- I am a good reader
- I learn more from reading than most students in the class

**Reading Challenge (5 items)**
- I like hard, challenging books
- If the project is interesting, I can read difficult material
- I like it when the questions in books make me think
- I usually learn difficult things by reading
- If a book is interesting I don't care how hard it is to read

**Reading Curiosity (6 items)**
- If the teacher discusses something interesting I might read more about it
- I have favorite subjects that I like to read about
- I read to learn new information about topics that interest me
- I read about my hobbies to learn more about them
- I like to read about new things
- I enjoy reading books about living things

**Reading Involvement (6 items)**
- I read stories about fantasy and make believe
- I like mysteries
- I make pictures in my mind when I read
- I feel like I make friends with people in good books
- I read a lot of adventure stories
- I enjoy a long, involved story or fiction book

**Importance of Reading (2 items)**
- It is very important to me to be a good reader
- In comparison to other activities I do, it is very important to me to be a good reader

**Reading Work Avoidance (4 items)**
- I don't like vocabulary questions
- Complicated stories are no fun to read
- I don't like reading something when the words are too difficult
- I don't like it when there are too many people in the story

Copyright© 2010 by John T. Guthrie. Not for use other than research purposes.

**Competition in Reading (6 items)**

- ☒ I try to get more answers right than my friends
- ☒ I like being the best at reading
- ☒ I like to finish my reading before other students
- ☒ I like being the only one who knows an answer in something we read
- ☒ It is important for me to see my name on a list of good readers
- ☒ I am willing to work hard to read better than my friends

**Recognition for Reading (5 items)**

- ☒ I like having the teacher say I read well
- ☒ My friends sometimes tell me I am a good reader
- ☒ I like to get compliments for my reading
- ☒ I am happy when someone recognizes my reading
- ☒ My parents often tell me what a good job I am doing in reading

**Reading for Grades (4 items)**

- ☒ Grades are a good way to see how well you are doing in reading
- ☒ I look forward to finding out my reading grades
- ☒ I read to improve my grades
- ☒ My parents ask me about my reading grade

**Social Reasons for Reading (7 items)**

- ☒ I visit the library often with my family
- ☒ I often read to my brother or my sister
- ☒ My friends and I like to trade things to read
- ☒ I sometimes read to my parents
- ☒ I talk to my friends about what I am reading
- ☒ I like to help my friends with their schoolwork in reading
- ☒ I like to tell my family about what I am reading

**Compliance (5 items)**

- ☒ I do as little schoolwork as possible in reading
- ☒ I read because I have to
- ☒ I always do my reading work exactly as the teacher wants it
- ☒ Finishing every reading assignment is very important to me
- ☒ I always try to finish my reading on time

**አባሪ ለ፡-** የተተኳሪ ተማሪዎችን የቅድመና ድህረ ትምህርት የማንበብ ተነሳሽነት ለመለካት ወደ አማርኛ ቋንቋ ተተርጉሞ አገልግሎት ላይ የዋለው የጽሁፍ መጠይቅ

**ውድ ተማሪዎች!** የዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማ "የአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂልን በትምህርታዊ ጨዋታዎች ስልት ማስተማር የተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነት ደረጃን ለማዳበር ያለው ሚና" በሚል ርእስ ለሚደረገው ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ በመሆኑም ይህን መጠይቅ ስትሞሉ ብትሳሳቱ በትምህርት ውጤታችሁ(ማርክ) ላይ ምንም አይነት ተጽእኖ አይኖረውም፡፡ ስለሆነም የእናንተ መጠይቁን በትክክል መሙላት ለጥናቱ ውጤታማነት አስተዋጽኦው የላቀ ስለሆነ በሙሉ ነፃነትና በትክክል እንድትሞሉት እጠይቃለሁ፡፡ ውድተማሪዎች ይህንን የጽሁፍ መጠይቅ በአግባቡ ሞልታችሁ ለመመለስ ፈቃደኛ ስለሆናችሁም ከወዲሁ አመሰግናለሁ፡፡

አሞላሉን በሚመለከትም በሠንጠረዡ የቀረቡ የማንበብ ተነሳሽነት ሃሳቦችን በጥንቃቄ በማንበብ ከፊትለፊት ከቀረቡት አራት የተነሳሽነት ደረጃ አማራጮች ውስጥ ከእናንተ የማንበብ ተነሳሽነት ጋር የሚስማማውን በመለየት የእራይት (✔) ምልክት አስቀምጡ፡፡

1. **በጣም አልስማማም** ☐ 2. **አልስማማም** ☐

3. **እስማማለሁ** ☐ 4. **በጣም እስማማለሁ** ☐

| ተ.ቁ | የማንበብ ተነሳሽነትን የሚገልጹ ዐረፍተነገሮች | የተነሳሽነት መለኪያዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 | 2 | 3 | 4 |
| | **የማንበብ ችሎታ/Reading Efficiency items/** | | | | |
| 1 | እኔ በጣም ጥሩ አንባቢ ነኝ | | | | |
| | **አዳዲስ ጽሁፎችን የማንበብ ጉጉት Reading Curiosity items** | | | | |
| 2 | መምህሬ አንድ አስደሳች ስለሆነ ነገር ከተናገሩ ስለዚያነገር ለማንበብ እጓጓለሁ | | | | |
| 3 | ሁልጊዜ ባነባቸው ደስ የሚሉኝ አጋዥ መፃሕፍት አሉኝ | | | | |
| 4 | ጥሩ ጥሩ ርእሶችን ሳገኝ አዳዲስ መረጃዎችን ለማግኘት ስል አነባለሁ | | | | |
| | **የንባብ ተሳትፎ /Reading involvement items/** | | | | |
| 5 | በክፍል ውስጥ የሚቀርቡ ምንባቦችን ሁልጊዜ ማንበብ ደስ ይለኛል | | | | |
| 6 | የተረት መፃሕፍትን ማንበብ በጣም ያዝናናኛል | | | | |
| 7 | ምንባብ በማነብበት ወቅት ሁልጊዜ ስለማነበው ነገር ምንነት በአእምሮዬ ምስል እፈጥራለሁ | | | | |
| | **ከንባብ የሚያርቁ ነገሮች/Reading work avoidance items/** | | | | |
| 8 | አስቸጋሪ ቃላት የበዙበት ምንባብ ሲገጥመኝ የማንበብ ፍላጎቴ ይቀንሳል | | | | |
| 9 | በክፍል ውስጥ የማነበው መምህሬ እንዳይቆጡኝ ስል ነው | | | | |
| | **የንባብ ውድድር/Compitition for reading items/** | | | | |
| 10 | በክፍል ውስጥ ስለአነበብነው ነገር ስንጠየቅ ትክክለኛ መልስ እንድመልስ እፈልጋለሁ | | | | |
| 11 | የሚነበብ የቤት ሥራ ሲሰጠኝ ፈጥኜ አንብቤ የቤት ሥራዬን መስራት ያስደስተኛል | | | | |
| 12 | ከጥሩ አንባቢዎች ስም ዝርዝር ውስጥ መግባት በጣም እፈልጋለሁ | | | | |
| 13 | በክፍል ውስጥ ሁሌ ከጓደኞቼ በተሻለ ትክክለኛ መልስ መመለስ እፈልጋለሁ | | | | |
| 14 | እኔ የማነበው በንባብ ጎበዝ ለመሆን ነው | | | | |
| | **በንባብ ችሎታ እውቅና ማግኘት/Recognition for reading items/** | | | | |
| 15 | ቤተሰቦቼ ሁሌም እንደማንበብ ያለ መልካም የእውቀት ምንጭ እንደሌለ ይነግሩኛል | | | | |
| | **ለውጤት ማንበብ /Reading for Grades items/** | | | | |
| 16 | እኔ የማነበው የፈተና ውጤቴን ለማሻሻል ነው | | | | |
| | **ለማህበራዊነት ሲባል ማንበብ/Social reasons for reading items/** | | | | |
| 17 | ሁልጊዜ በቤት ውስጥ ለቤተሰቦቼ ምንባብ አነብላቸዋለሁ | | | | |
| 18 | ስለማነበው ነገር ለቤተሰቦቼ ገለፃ ማድረግ ሁሌም ያስደስተኛል | | | | |
| | **አሟልቶ ማንበብ /Compliance reading items/** | | | | |
| 19 | እኔ የማነበው ተማሪ ስለሆንሁና ማንበብ ስላለብኝ ነው | | | | |
| 20 | ሁልጊዜ የማንበብ ሥራ ሲሰጠን ፈጥኜ አንብቤ ለመጨረስ እሞክራለሁ | | | | |

**አባሪ ሐ፡-** ስለጽሁፍ መጠይቁ አስተማማኝነት በዊግፊልድ እና ጉዝሪ (1997) ከቀረበ የጥናት ውጤት ለማሳያነት የቀረበ

| | |
|---|---|
| | 8. Recognition for Reading (5 items)<br>9. Reading for Grades (4 items)<br>10. Social Reasons for Reading (7 items)<br>11. Compliance (5 items) |
| **Scoring/ Reporting** | The response format for the above items is 1 = *very different from me* to 4 = *a lot like me*. Scores are computed for each aspect and construct by averaging across their respective items. |
| **Reliability** | Wigfield and Guthrie (1997) reported the reliabilities for all the aspects of the 53-item MRQ ranging from .43 to .81. Work Avoidance and Reading for Grades had reliabilities of .44 and .43, respectively, at one time point, but they had reliabilities of .60 and .59 at a different time point. The remaining 9 aspects showed consistent reliabilities ranging from .52 and .81. |
| **Validity** | Factor analyses conducted by Wigfield and Guthrie (1997) indicated evidence of construct validity supporting eleven factors for the 53-item revised MRQ in 4th and 5th grade students. Most of the reading motivation aspects correlated positively from low- to moderately high levels, providing further evidence of construct validity. Only the Work Avoidance aspect correlated negatively with all aspects aside from Competition in Reading. Unrau and Schlackman (2006) also found support for the 11-factor model in a sample of 6th, 7th, and 8th grade students with a confirmatory fit index (CFI) of .90, suggesting relatively good model fit. |
| **Overview of Use** | The MRQ has been used in published research by the instrument developers to explore the multi-dimensionality of student's reading motivation in grades 4-5 and to assess the impact of the CORI intervention on reading motivation in 3rd grade students. The MRQ has also been successfully used in published research by other researchers with middle school students from grade 6-8. |

| | |
|---|---|
| **Name of Instrument** | **Motivations for Reading Questionnaire (MRQ)** |
| **Developer/ Website** | The items were developed by Dr. Allan Wigfield and Dr. John Guthrie at the University of Maryland. |
| **Instrument Availability/ Key Source(s)** | The items are described in the following published article in which the authors indicate that the items and format for the instrument are available by contacting them.<br><br>Wigfield, A. & Guthrie, J.T. (1997). Relations of children's motivation for reading to the amount and breadth of their reading. *Journal of Educational Psychology, 89*, 420-432. |
| **Population** | Wigfield and Guthrie (1997) used the MRQ on a sample of 105 4th and 5th grade elementary students at one mid-Atlantic state school and 148 (Guthrie et al., 2004) and 150 (Wigfield et al., 2004) 3rd grade students from four mid-Atlantic state schools (respectively) during administration of Concept-Oriented Reading Instruction (CORI; see www.cori.umd.edu for more details). The student samples were approximately 70-76% European American and 22-30% African American.<br><br>Unrau and Schlackman (2006) also used the MRQ successfully with a sample of 2000 6th, 7th and 8th grade middle school students from one school in the Los Angeles area. This sample of middle school students was 75% Hispanic, 20% Asian, and 5% African-American, American Indian or White. |
| **Type of Method** | Student ratings of various aspects of their reading motivations. |
| **Overview** | The Motivations for Reading Questionnaire is a student rated assessment of the extent to which each student is motivated to read. It was originally developed by Wigfield and Guthrie (1995) to assess different aspects of student's reading motivation. In 1997, Wigfield and Guthrie improved the MRQ by grouping questions into 11 constructs of reading motivation with the help of motivational interviews with students, classroom reading instruction observations (Guthrie et al., 1996), and alignment with motivational theory. The original scale contained 82 items (Wigfield & Guthrie, 1995), but was revised by Wigfield and Guthrie (1997) and now only contains 53 items. A shortened version (18 items) of the MRQ was also created to use for pre- and post- CORI assessments (Guthrie et al., 2004; Wigfield et al., 2004). |
| **Administration** | The MRQ is a set of items that each student completes independently with a group of other students (approximately 10-15). As a group, students go through 3 practice questions with the questionnaire administrator(s) and then are allowed to complete the remainder of the questionnaire on their own. The revised MRQ only has 2 practice questions. Questionnaire administrators are available to answer questions during this time. Students are typically able to finish the MRQ in one 15 to 20 minute session (Wigfield & Guthrie, 1997). |
| **Domains Measured** | The revised MRQ contains 53 items intended to reflect 11 constructs of reading motivation:<br><br>1. Reading Efficacy (3 items)<br>2. Reading Challenge(5 items)<br>3. Reading Curiosity (6 items)<br>4. Reading Involvement (6 items)<br>5. Importance of Reading (2 items)<br>6. Reading Work Avoidance (4 items)<br>7. Competition in Reading (6 items) |

Copyright© 2010 by John T. Guthrie. Not for use other than research purposes.